*ህይወታቸው አልፏል:: ከሚታወቁት አንዱ፣ አጋፊሪ ጎለም ነበር:: ወረርሽኙን መቋቋም የቻሉት ጦራቸውን በየቦታው ከፋፍሎ በማስፈር ነበር::*

***ቀጥር 59፤*** *እዚህ ላይ የታሠሩ አውሮፓውያን ቤተሰቦችን እወክላለሁ በማለት በራሱ አነሳሽነት የመጣ ዶክተር ቤክ የሚባል ሰው ነበር:: የመጣበት ጊዜም፣ ቴዎድሮስ እስረኞቹን ለመፍታት ቃል በሠጡበት ጊዜ ሲሆን፣ የሰውየው ተልኮ በተቃራኒ፣ ቴዎድሮስ በአውሮፓውያን ላይ የነበራቸውን ጥርጣሬ አባብሶታል:: የዶክተር ቤክን ግልቃ ገብነት እነራሳምም አልወደዱትም ነበር:: ሰውየው ወደ ትግራይ ዘልቆ ለንጉሡ መልክት ሲልክ፣ ያለኔ ፈቃድ ማን ሀገሬ ውስጥ ግባ አለህ በማለት ወደ ምፅዋ እንዲመለስ አድረገውታል:: የሰውየውን ባህሪ በትክክል የሚያውቀው አቶ ሳሙኤል ሲናገር፣ ዶክተር ቤክ እንግዳ የሆነ ባህሪ አለው፤ ቢመጣ ኖሮ፣ ቴዎድሮስ በሁለተኛው ቀን እስር ቤት ያስገቡት ነበር ብሏል::*

***ቀጥር 60፤*** *አቢሲኒያ ብሉ ቡክ፣ የእንግሊዝ መንግሥት ስለ አቢሲኒያ ማንኛውንም ዘገባ ጥናት ወይም ታሪክ እየሰበሰበ የሚያስቀምጥበት ፋይል ነው:: ይህ ፋይል የደብዳቤዎች ቅጅ ሳይቀር ይሰበሰብበታል:: በዚያን ጊዜ የእንግሊዝ መንግሥት ስለ አቢሲኒያ ሁኔታ ጠንቅቆ ማወቁ የመቅደላን ዘመቻ የተሳካ እንዲሆን አድርጎለታል:: የሚገርመው ነገር፣ እንግሊዛውያን ብቻ ሳይሆን ሌሎች አውሮፓውያን የሚዘግቡትም ይሰበሰባል:: በመቅደላ ዘመቻ፣ ፈረንሳዊው መንዚንጀር ከናፒየር ጦር ጋር ዘምቶ፣ ዋግ ሹም ጎበዜን ማግባባት የቻለው እሱ ነበር:: አውሮፓውያውያ እርስ በርስ የሚፎካከሩ ቢመስልም በእንደዚህ አይነቱ ጊዜ ግን ሲተባበሩ ነው የሚታየው::*

# ምዕራፍ ሁለት

## አነስሊ ወሽመጥ - ኮሎኔል መርዌዘር

አነስሊ የባህር ወሽመጥ የተፈጠረው፣ ዲሲ[61] በሚባል ከአቢሲኒያ ድንበር ጋር በትይዩነት ለሀያ ማይሎች በተዘረጋ ደሴት ነው:: በመሀሉ የሚገኘው ይህ ወሽመጥ ከአንድ እስከ አምስት ማይሎች የሚሆን የጎን ሰፋት አለው::

ለዚህ አይነቱ ሥራ ከኮሎኔል መርዌዘር[62] የበለጠ ምርጫ ሊኖር አይችልም:: ኮሎኔሉ፣ በህንድ በፈረሰኛ መኮንንነት ሲያገለግል የነበረና አሁን ደግሞ በኤደን ተቀማጭ የፖለቲካ ሠራተኛ ነው:: ይህ ሰው፣ ቀድሞ ከሆርመዝ ጄ ራሳም ጋር በነበረው ትውውቅም ሊሆን ይችላል የሰውየውን መታሰር ሲሰማ ለማስልቀቅ ተነሣሣ:: ለእስረኞቹ የሚሆን ገንዘብ ላከ፤ አቢሲኒያውያንን በጉቦ በመደለል ወደ መቅደላና ደብረ ታቦር መልከት መላክ ጀመረ:: በሎንደን ለነበሩ ዋና ጋዜጦች የጋዜጣ አንቀፅ መፃፍ ጀመረ፤ በፅሁፉም፣ ታላቋ ብሪታኒያ በህንድ ሲደርስባት ከሚችለው ውርደት ራሷን ማዳን አለባት አለ፤ ይህ የእንግሊዝ መልከተኞች በመቅደላ በእስር መያዛቸው፣ በመሀመዳኑና በሂንዱስታን ሰዎች ከተሰማ፣ በምስራቅ በሚገኘው የንግስቲቷ ግዛቶች አለም አቀፍ አመፅ ሊነሳ ይችላል::

መርዌዘር፣ አይነተኛ የሆነ መኮንን፤ በምስራቅ በኩል በተደረጉ የተለያዩ ጦርነቶች፣ ጎበዝ፣ ሰልት አዋቂ፣ ደፋርና ፈጣንነቱን ያስመሰከረ ሰው በመሆኑ፣ አቢሲኒያ ደንበር ላይ ለሚሰፍረው ለመጀመሪያው ጦር አዛዥ እንዲሆን ተመረጠ:: ከዚህም ጋር የሀገሪቷን ተወላጆች በመጠየቅ ወደፊት ይከሰታሉ የሚባሉ ችግሮችን እንዲመረምርና ወደ መሀል አገሪቱ መግቢያ መንገድ እንዲፈልግ ነበር:: ወጣትና ሙሉ ጉልበት ያለው ሰው በመሆኑ ለማረፊያ የሚሆነውን ቦታ ፈልጎ ሲያገኝ ጊዜም አልወሰደበትም:: በዚህ፣ በእጁ ባደረገው መስፈሪያ ቦታም የቅዱስ ጊዮርጊስ ምስል ያለበት መስቀል በራሱ አፎ ለመጀመሪያ ጊዜ ተከለ::

---

61 ደሴቱን ደጃች ንጉሴ ለፈረንሳዮች በሥጦታ (በምዕራፍ ሁለት ማስታወሻዎች)

62 ኮሎኔል መርዌዘር፣ ቴዎድሮስ የጠየቋቸውን (በምዕራፍ ሁለት ማስታወሻዎች)

ወሽመጡን የሚዋሰነው የአቢሲኒያ ደንበር አሸዋማ የሆነ የባህር ዳርቻ ሲሆን፣ ከአስራ አራት እስከ አስራ አምስት ማይል ስፋት ያለው፣ በሰሜን ሀያ ማይል ርዝምት እስከ ምፅዋ፣ በደቡብ ደግሞ እስከ አነስሊ ወሽመጥ የተዘረጋ ነው:: በዚህ ከወሽመጡ መግቢያ ሶስት አራተኛ ርቀት ጀምሮ፣ በደቡብ በአሸዋማው ዳርቻ፣ ከዙላ ወደብ ለመድረስ አራት ማይል ርቀት ባለው ስፍራ፣ ሌፍተናነት ኮሎኔል መርዌዘር ጠቅላይ ፅሀፈት ቤቱን መሠረተበት:: ከዚህ የባሰ አስቸጋሪ ቦታም አልተመረጠም:: ነገር ግን፣ ይህ ቦታ የተመረጠበት ሁለት ምክንያቶች ነበሩት:: አንደኛው ጥልቅ የሆነ ወሽመጥ በማዋሰኑ፣ ከባህር በኩል የጦር መሣሪያ በቀላሉ ሊራገፍበት ይችላል:: ሁለተኛ፣ በሁለት ከፍተኛ ቦታዎች መሀከል ርዝመት ያለው ክፍተት ቦታ በመኖሩ፣ ወደ መሀል አገር ቀላል መግቢያ ጋር ስለሚያገናኝ ነው:: የዚህ ወደ መሀል ሀገር መግቢያ ክፍት ቦታ ከመርዌዘር ፅሕፈት ቤት በምዕራብ አቅጣጫ አስራ አምስት ማይሎች ርቀት ላይ ይገኛል::

በዚህ ቦታ እንደሰፈረም፣ ኮሎኔል መርዌዘር፣ ለቦምቤዩ ገዥና በሎንደን የህንድ ፅሕፈት ቤት ለሰር ስታፈርድ ኖርዝኮት፣ ስላደረገው ከፍተኛ አሰሳ፣ የቦታ ፍለጋና ስለተገኘው ጥሩ ውጤት ደብዳቤ ይልካል:: ያለ ዕድል ሆኖ፣ ስላገኘው ቦታ ከሚገባው በላይ አጋኖ ነበር የገለፀው:: እንደ አገላለፁ፣ እንጨትና ውሀ እንደልብ እንደሆነ፣ ሳር ከሚበቃ በላይ መኖሩን፣ ደኑም ቢሆን የሚያዝናና፣ ወደ መሃል አገር መተላለፊያው ቀላል መሆኑን፣ ስፍራው ለአደን የሚሆኑ የተለያዩ እንስሳት ሀብት እንዳለው ነበር::

የኮሎኔሉን መልክት እንደተቀበሉ፣ ሁለቱ ሰዎች፣ ከሎንደን የህንድ ፅሀፈት ቤትና የቦምቤይ ባለሥልጣኖች ወደዚህ ብሩህና መንግስተሰማይ የመሰለ አገር ለመጓዝ ለመዘጋጀት መምከከር ጀመሩ:: ሌፍተናንት ጄኔራል ሰር ሮበረት ናፒየር የጦሩ አዛዥ እንዲሆን ተመረጠ:: በእርሱ ትዛዝና ምክር መሠረት ለዚህ ዘመቻ መቃናት ይሆናል ያለው የሰዎች ቁጥር ተወሰነ:: ከተለያዩ የጦር ክፍሎች የመጡት ሰዎች ጉዞ ከመጀመራቸው በፊት በቦምቤይ እንዲሰበሰቡ ተደርጎ በየከፍል አዛዦች ግምገማና አብሮም የጋለ ማበረታቻ ንግግር ተደረገ::

ከቦምቤይ ሀላፊዎች በጣም ብዙ ሲጠበቅ ስለነበር፣ በጉጉት፣ የጥቂት ቀናት ሰንቅ ብቻ በማስያዝ ጦሩን ወዲያውኑ ወደ ዙላ የመላክ ምኞት ነበራቸው:: ሊያዝ የታቀደው ስንቅም ረሃብ ሊያስከትል በሚችል ሁኔታ መጠኑ ያነሰ ነበር:: ሆኖም ነገሮችን በጥሞና የመመልከት ፖሊሲ ባይኖር ኖሮና፣ በሰር ሮበርት ናፒየር ለእንደዚህ አይነቱ ትርጉም የለለው የሲቪሊያኖች አቀራረብ ጠንካራ ተቃውሞ ባይደረግ፣ ከፍተኛ የሆነ ጥፋት በተከተለ ነበር::



ቀዳሚው ብርጌድ፣ በውስጡ የዋናው አዝ ከንፍ ስስተኛው ቀላል ፈረሰኛ ክፍል፣ 10ኛው የቦምቤይ የተወላጆች[63] አግረኛ ጦር፣ 3ኛና 4ተኛ ኮምፓኒ፣ እና የተወላጆች (ህንድ) ምሽግ ቆፋሪዎችና ካምፕ አዘጋጆች ያሉበት ዙላ ሠፈረ::

ይህ ከፍልም የጦር ካምፑ ዋና ጠባቂ እንዲሆንና ወደፊት ተከትሎ ለሚመጣው ጦር አስኳል እንዲሆን ታስቦ ነው:: ከዚህ ብርጌድ ጋር፣ ሁለት ዘጋቢዎች፣ ከታዋቂ የእንግሊዝ መፅሔቶች ከታይምስና ከደይሊ ኒውስ ነበሩ:: ከታይምስ የመጣው ዘጋቢ የደረሰበት መከራ በዚሁ መፅሔት ላይ ስዕላዊ በሆነ አገላለጥ በአምዶቹ ላይ ተፅፎ አልነበረምን?


ዙላ ካረፉት አንዱ ብርጌድ ወሽመጡ እንደደረሰ፣ ብዛት ያላቸው የባህር ማመላሻዎች ያመጧቸውን በሺ የሚቆጠሩ በቅሎዎች፣ ግመሎችና የቀንድ ከብቶችን፣ በቅሎ መሪዎችና ከብት ጠባቂዎች ሳይኖሩ እንዲሁ ለቀቋቸው:: እንስሶቹ፣ ከባህር ጉዞ በኋላ ከወደቡ ሲለቀቁ ግጦሽና ውሀ ፍለጋ ምንም ሳያገኙባቸው አካባቢውን ይራወጡትበት ጀመር:: ሣርና ውሀም ባለማግኘታቸው በየቁጥቋጦውና ጫካው ሲርመሰመሱ በየገደሉ እየወደቁ በመቶዎች የሚቆጠሩ ይሞቱ ጀመር:: ብዛት ያላቸውም ይሠረቁ ጀመር፤ ብልጣ ብልጥ የሆነ የፈረሰ ደላላ ምፅዋ ላይ መርከብ ይዞ ቢጠብቅ፣ የመጡትን በቅሎዎችና ግመሎች ከወረዱበት ከአቢሲኒያ ምድር ወድያውኑ እንደአመጣጣቸው በፍጥነት መልሶ ወደ ህንድ በወሰዳቸው ነበር::

ከሁለት እስከ ሶስት ሺ የሚቆጠሩ እንስሶች ሲሞቱ፣ የጦሩ አዛዥ ለዚህ ጥፋት መላ መፈጠር የሚያስፈልግ መሆኑን ተገነዘበ፤ እሱም በቀላሉ የሚሰራ ሆኖ ነው የተገኘው::[64]

በእንፋሎት የሚነዳው የውሃ ላይ ማመላለሻ በባሕሩ ወሽመጥ እንዲቆይ ተደርጎ ውሀ እያፈላ በእንፋሎት የሚወጣውን ውሀ እያቀዘቀዘ እንዲያጠራቅም ተወሰነ:: ለዚህም፣ ጀልባዎች ወደ ህንድ ተልከው ለዚህ ስራ የሚሆኑ እንፋሎት የሚያቀዘቅዙና የሚሰብሰቡ በአስራዎች የሚቆጠሩ መሳሪያዎችና ብዛት ያላቸው የአሜሪካ የኖርተን የውሀ ፓምፖች እንዲያመጡ ተደረገ::

[63] ተወላጆች የሚለው የህንድ ሰዎችን ነው::

[64] በመርከብ የመጡት እንስሳት ቁጥር፤ 2,538 ፈረሶች፣ 44 ዝሆኖች፣ 17,673 በቅሎና የጫኑት ፈረሶች፣ 5,735 ግመሎች፣ 1,759 አህዮች፣ 7,071 ድልብ በሬዎች ነበሩ:: ከሀገሩ ሰዎች ደግሞ 270 በቅሎዎች፣ 1,004 በሬዎች ነበሩ:: ባጠቃላይ የእንስሳቱ ቁጥር 36094 ነበር:: (Record of The Expedition to Abyssinia)



*በዙላ የውሀ ማጠጫ ገንዳዎች*
(ዋቢ መፅሐፍ ተ.ቁ. 16)



እነዚህ መጓሪያዎች እንዲመጡ ትዛዝ ከተሠጠ ከሶስትና አራት ሳምንታት በኋላ መጓሪያዎቹ ዙላ ደረሱ፤ ከነሱም ጋር በሺ የሚቆጠሩ (coolies, ኩሊያዎች[65]) የቀን ሠራተኞች አብረው መጡ:: የኋለኞቹ፣ ወድያውኑ ሌሎች የሚመጡትን ከባድ ጓዞች ለመቀበል የወደብ ክፍሎችንና የውሀ መውረጃ ገንዳዎችን ሥራ እንዲጀምሩ ተደረገ:: የዚህ ሥራም በሚገርም ፍጥነት በአጭር ጊዜ ውስጥ ተጠናቀቀ:: ለአንደኛው ትልቅ ውሀ ማጣሪያ በድንጋይ ደሴት ተሠራለት፤ የተጣራውን ውሀ ለማውረድ ከደሴቱ ወደ መሬቱ የውሀ መውረጃ መስመር ከተሠራለት በኋላ፣ የተጣራውን ውሀ ከባህሩ ዳርቻ ባሉ ውሀ ማጠራቀሚያዎች በማጠራቀም ለአገልግሎት እንዲውል ተደረገ::

እነዚህ፣ አዲስ፣ በመርከብ ከሰዊዝ እየተጫኑ የሚመጡት እንሰሳት ከስፔይን፣ ከጣልያን፣ ከሶርያና ከግብፅ ነበር የተሰበሰቡት፤ ከነዚህ ጋር ደግሞ የቱርክና አረብ በቅሎ መሪዎች አብረው መጡ:: ይህ ደግሞ ሌላው የሚያሳዝንና ብልሃት የጎደለው ትዛዝ ነበር::

ማንም፣ ከነዚህ ሰዎች ጋራ የሥራ ግንኙነት የነበረው መንገደኛ በደንብ የሚያውቀው ነገር ቢኖር፣ ቱርኮችና አረቦች በጣም አስከፊ የሆነ፣ ከሰው ጋር የማይገጥምና የሚበጠብጥ ባህሪ እንዳላቸው ነው::

ወድያውኑ፣ በኮሎኔል መርዌዘር ሥር ደጋማዋን ቦታ ለመያዝ ወደፊት የሚገሰግሱት ወታደሮች፣ ጓዛቸውና ጓዙን የጫኑት እንስሳት ከመሪዎቻቸው ጋር መጥፋታቸው ተነገራቸው::

በጀምላ፣ የሰዎችና የከብቶቹ መጥፋት ሁኔታ በየቀኑ ይከሰት ነበር:: በየክፍሉ የሚገኙ የቀዳሚው ጦር አዛዦች በየጊዜው የሚጠፋውን ንብረትና ሰው ቁጥር በተረዱ ጊዜ፣ የታጠቁና በሥነሰርአት የሚጓዙ ወታደሮች፣ ከዘመቻው በተጨማሪ ለሌላ ሥራ የሚያስፈልጉ መሆኑን በመረዳት፣ ከጓዙና ከሰዎች ጀርባ ጥቂት የታጠቁ ወታደሮች መድቦ እንዲጠብቁ ማድረግ አዋቂነት የተገባው ተግባር መሆኑን ተገነዘቡ::

እንዲህ ያለው የሥራ ልምድ ከብዙ ኪሣራ በኋላ የሚገኝ ነገር ነው የሆነው:: የእንግሊዝ ሠራዊት በቦምቤይና በቻታም በካምፕ ሠፍሮ ለብዙ ጊዜ ስለኖረ ለዘመቻ የሚያስፈልጉ ብዙ የሚደረጉ ነገሮች መኖራቸውን ዘንግቷል::

በዙላ፣ የወታደሮች ቁጥር በፍጥነት እየጨመረ ነበር:: ወደፊት ያለው መንገድ ወይም ማለፊያ በር ከተቃኘ በኋላ፣ ሰር ቻርልስ ስታቨሊ የተባለው ጄኔራል፣ ማለፊያው በር መጨረሻ ላይ በከፍተኛው ቦታ የሚገኝ፣ ሰናፌ

65 ይህ ቃል በቻይናና በአካባቢው አፀያፊና ከሰድብ የሚቆጠር ነበር:: በኢትዮጵያም በተለይ በአዲስ አበባ ለተወሰነ ጊዜ ይህን ቃል ህዝቡ ሲጠቀምበት ነበር::

የሚባል መንደር እንዲያዝና ወደ መቅደላ በሚደረገው ዘመቻ ሁለተኛው ዴፖ ካምፕ(ከዙላ ቀጥሎ) እንዲሆን ያዛል፡፡ በመርዌዘር የሚመራ ጦር ስናፌን ለመያዝ መንገድ ላይ ነበር፡፡ በኋላም በቀረበው ሪፖረት፣ በስናፌ በቂ ውሀ እንዳለ፣ አየሩም ጤናማ መሆኑን፣ በቂ ሳር እንዳለ፣ ገለባ፣ እጃና ገብስ ከነዋሪዎች ማግኘት የሚቻል መሆኑ ሲታወቅ፣ የጦሩ አብዛኛው ክፍል ወደ ስናፌ እንዲዛወር ተደረገ፡፡



ኮሎኔል መርዌዘር

ወደ ደጋማው ክፍል ማስፈያው ከብዙ ጉልበት ሥራ በኋላ፣ በማወዳደር ሲታይ፣ ቀለል ባለ ሁኔታ ሊጠናቀቅ ተችሏል፡፡ እንባቢዎች በደንብ እንዲረዱትና አገላለፁ ቀለል ያለ እንዲሆን፣ እኔ የምገልፀው የቁማይሌ ማለፊያ ከላይ ከባሕር ወለል በላይ 7ሺ ጫማ ከሚገኘው ስናፌ ከተለያዩ ተራራማዎች በሚወርዱ የጎርፍ ወራጆች የተፈጠረ ሸለቆ ነው፡፡ ይህ ማለፊያ[66] ወይም ሸለቆ ቁልቁል እየወረደ በክረምት ጊዜ በመሙላት ሀይለኛ ወራጅ ውሀ

[66] (በምዕራፍ ሁለት ማስታወሻዎች)



የሚፈጥረውን ወንዝ በመከተል ከ63 ማይል ርቀት በኋላ ዙላ ወደብ ላይ ያቆማል፡፡

ሆኖም በበጋ ወራት ደረቅ ስለሆነ፣ ሙሉውን የወንዙን ርዝመት፣ መንገደኞች በእግራቸው ያልፉበት ነበር፡፡ በደረቀው ወንዝ ዳካ የነበረ ነገር ቢኖር፣ ከላይ ከከፍታማ ቦታዎች የወረዱ አለቶችና የእንጨት ቅርንጫፎችና ስብርባሪዎች ነበሩ፡፡ ለወታደሮቹ ማለፊያ፣ በጣም ከፊት ያለውን የማያስቸግር ስፋራ በመመረጥ የተሽከርካሪ መሄጃ መንገድ እንዲሆንም ተደረገ፤ ነገር ግን በአንዳንድ ጠባብና አስቸጋሪ ቦታዎች አለቱን በመቁረጥ መንገድ መሥራት ነበረበት፡፡ በነበራቸው አጭር ጊዜ ውስጥ ባወጡት ዕቅድ፣ ከዚህ የተሻለ መንገድም አይሰራም ነበር፡፡ ስለዚህ የዚህ ሥራ ሃላፊ ስነበሩ መሀንዲሶች ትልቅ ምስጋና መስጠት ተገቢ ነበር፡፡ ወታደሮች፣ ጓዝ፣ እንስሳት፣ ከባድ መሳሪያው እና ተሽከርካሪዎች በተመቸ ሁኔታ ከፍ ባለ ቦታ ወደሚገኘው ወደ ስናፌ መጓዝ ቻሉ፡፡

በሁለት ወራት ውስጥ፣ ወደፊት ለሚደረገው እንቅስቃሴ ሁሉም ነገር ዝግጁ ነበር፤ እናም ሰር ሮበርት ናፒየር ደረሰ፡፡ የተሠራውን ሁሉንም ነገር፣ የተሠሩትን መካዝኖች፣ ውሀ ማጣሪያዎች፣ የባቡር ሀዲዶች፣ የወደብ ክፍሎች ከጎበኘ በኋላ፣ ቀዝቀዝ ያለ ነፋሻማ አየር ወዳለበት ወደ ስናፌ ተሻገረ፡፡

አጭር፣ ወደ አምስት ማይል ርዝመት ያለው ሀዲድ ከዙላ ወደብ እስከ ካምፑ ጠርዝ ድረስ ተዘርግቷል፡፡ ሁለት ባቡሮች ከባሀር ወርደዋል፤ እነዚህም ብዙት ያለውን ወደቡ ላይ እየተራገፈ በየቀኑ በፍጥነት የሚከማቸውን ጓዝ ወደሚመች ቦታና ወደየጦር ክፍሉ በማመላለስ ትልቅ አስተዋፅኦ ነው ያደረጉት፡፡

አቢሲኒያ በደረስኩ በማግስቱ፣ በካምፑ ውስጥ፣ ማንም ሰው ገና ዝር ሳይል፣ እኔና ሠራተኛዬ አሊ በጠዋት ተነስተን ዙላን ለቀን ጉዞውን በመልካም ሁኔታ ጀምረናል፤ ሆኖም ለጉዞው የሚሆን የሚበቃንን ቁሳቁሶች አልያዝንም፡፡

በሀሳቤ የነበረው፣ የኔ፣ የአቢሲኒያና የእንግሊዞች ዘመቻ አመለካከት ያልተጠና ነበር፤ ይህም ያለ ምንም ጥርጣሬ ወደፊት በምናደርገው እንቅስቃሴ በደንብ ይገለጣል፡፡

ከዙላ እስከ ቁማይሌ የነበረው ርቀት አስራ አራት ማይሎች ነበር፡፡ የዙላን ካምፕ እንደጨረሱ መንገዱ በረሃና አሸዋማ ነው፤ አልፎ አልፎም በተለያዩ የተከል አይነቶች የተሞሉ ችፍግ ያሉ ቁጥቋጦዎች ይታዩበታል፡፡

ተወላጆቹ የሚኖሩበትን የዙላን መንደር ካለፍን በኋላ፣ ደናግ[illegible] ያልታረሱ፣ አጠር ባሉ ቁጥቋጦዎች የተሸፈኑ ጉብታዎች መውጣት ጀመርን። በጉብታዎቹ፣ በክረምት ወራት እንደልቡ እየጎረፈ የሚወርደው ውሀ የሸረሸራቸው ከፍተቶች አልፎ አልፎ ይታያሉ። እንደገናም በዝናቡ ወራት የሚያፈልቁ አሁን ግን የደረቁ ደቦልቦል ባሉ ድንጋዮች የተሞሉ የምንጭ ቦታዎችን አናያለን፤ ከዚያ ደግሞ ዳገት የግድ መውጣት ነበረብን፤ ከትንሽ ጊዜ በኋላ እንደገና አፈር ብቻ ወይሆን ጎድጓዳ ቦታ ቁልቁል መውረድ ነበረብን። የውሀ ጠብታ የሚባል የትም አይታይም። በኋላ፣ በቁማይሌ እንደተረዳነው፣ ለመጠጥ የሚሆን ውሀ በባህሩ ዳርቻ እንደማይገኝ ነበር። ኮሎኔል መርዌዘር በቂ የሚጠጣ ውሀ አለ ብሎ ሪፖርት ሲያደረግ፣ በጣም በስህተት ተመርቶ ነበር፤ ምክንያቱም በዝናቡ ወራት የነበረው ውሀ እርሱ ከመድረሱ በፊት ደርቆ ነበር።

አንዳንድ ቦታዎች የተቋሩ ውሀዎች አግኝቶ ነበር፤ እነሱም ቢሆን በጥቂት ቀናት ውስጥ እንዳለ ከአይን ነው የተሰወሩት፤ ምክንያቱም ቦታው አሸዋማ ስለነበር የነበረውን እርጥበት እንኳን ወደ ውስጥ ስቦታል።

በግምት፣ ከአሰቸጋሪ የአምስት ሰአታት ጉዞ በኋላ ከተራራ ስር ደረስን፤ ከተራራው አናት ላይም የቁማይሌ ካምፕ መታየት ጀመረ። በዚህ ቦታ ነው እንግዲህ ተራራውን ከሁለት ከፍሎ ወራሪዎችን ወደ አቢሲኒያ የሚያስገባው ማለፊያው በር ያለው።

ትልቅ ሰፋ ያለ ከፍተት በጎንና በጎን በተራሮች ሰንሰለት ታጅቦ ይታያል፤ ተራሮቹም በቁጥቋጦና በቁልቋል ተከሎች ተሸፍነዋል። አልፎ አልፎ የአየር ፀባዩ የተፈራረቀባቸው ግራጫ መልክ ያላቸው አለቶች ከጋራዎች ጎን ብቅ ብቅ ይላሉ። አለቶቹም ቢሆን ደመቅ ያለ አረንጓዴ ተከሎችና ከአለቶቹ ጎን በበቀሉ ተከሎች መሀል ነው ፈጠጥ ብለው የወጡት። ቀረብ ካሉት የጋራ ሰንሰለቶች በላይ፣ ሌሎች፣ ተለቅና ሰፋ ያሉ ተራራዎች፣ አሻቅበው ሲመለከቷቸው እናታቸው ደመናውን የሚለሙ መስለው ይታያሉ። እነዚህ ከፍ ያሉት፣ ሌሎቹን፣ እንደቲያትር ቤት አዳራሽ መድረክ አካበውና አቅፈው ሲታዩ፤ በመሀሉ፣ ማለፊያው መንገድ ጠቆርና ጨለም ብሎ ይታያል።

ካምፑ ያለበት ቦታ ከብነቱ ሰስት እራተኛ በሆነ ሰፍራ ላይ ነው ። ሁለት ተለቅ ያሉ ኮረብታዎች በካምፑ ዳርና ዳር እንደጠባቂ ወይም ተከላካይ ዘብ ቆመው ይታያሉ። እነዚህ ሁለት ትልልቅ ኮረብታዎች ደግሞ፣ ጠበብ ባለ የተራራ ሰንሰለት ከነዚያ ከትልቆቹና ሰፋፊ ተራሮች ጋር የተገናኙ ናቸው። አዳራሽ ወደመሰለው ቦታ ከማምራታችን በፊት፣ የመጣንበትን አካባቢ ለማየትና ባህሩንም ለመሰናበት ወደ ኋላ ዞረን ተመለከትን። ማንም መገመት የማይችለው ብሩህ እይታ ነበር። ከግርጌያችን፣ አሸዋውን ከእይታ በደበቁ




ቁጥቋጦዎች የተሞላ ሜዳማ ቦታ ይታያል። ደመቅ ካለ [illegible] የሚያብረቀርቅና [illegible] አሸዋ፣ ከዚያ ቀጥሎ ደግሞ የተበታተኑ የበረዶ ከምሮች የመሰሉ [illegible] ድንኳኖች፣ ከዚያ አለፍ ብሎ ደግሞ መልሀቃቸውን የጣሉ ግርማ [illegible] ያላቸው መርከቦች በወሽመጡ ይታያሉ። አየሩ ግልፅና ለማየም ደመና ሰላልነበረው፣ የእያንዳንዱ መርከብ ሸራና ገመዶች ተለይተው ይታያሉ፤ ከዚያም በራሳቸው ተከልለው በአኩለ ቀኑ ፀሀይ ስር የሚያንቀላፉ [illegible]። አለፍ ብሎ የሚታየው ደግሞ የዲሴ ደሴት ነበር። ካለንበት ከፍታ ሆኖ አይናችን ከደሴቱ ጀርባ ሰማያዊና ፀጥ ያለውን ከአድማሱ ባሻገር የተሸሸገውን የቀይ ባህርን መቃኘት ይችላል። ካለንበት በግራ በኩል ወደ ሀያ [illegible] ርቀት፣ በአረንጓዴ ዛፎች መሀከል የተኮለኮሉ ጠፍጣፋ ጣራ ያላቸው ቤቶች ያሉበት የምፅዋ ከተማ ለእይታ ይገባል።

ወደፊታችን ከትንሽ እርምጃዎች በኋላ፣ ጨለማ በሆነው ማለፊያ ውስጥ ገብተን ተሠወርን፤ በከለሉን ኮረብታዎቹ አማካኝነት ቤታችን ነው ብለን ከምናስበው፣ ከጓደኞቻችንና ከሥልጣኔ ጋራ ተለያየን።

የአሜሪካ ኖርተን ፓምፖች በቁማይሌ ተአምር ነው የሠሩት። ውሀ በየቦታው ነው የሚገኘው። የደከሙት ግመሎችና በቅሎዎች ይህን ውድ መጠጥ እንደልብ ነው ያገኙት። ካምፑን ዙሪያዎን በከበቡት ከፍታዎች ምክንያት፣ በተፈጠረው ጥላና ከተራሮቹ ቁልቁል በሚነፍሰው ንፁህና ቀለል ያለ አየር ምክንያት በፍጥነት ነው ያገገሙት። ዙላ ለሳምንታት ሲቆዩ፣ ሰውነታቸው የተጎሳቆለውና የደከመው ህመምተኞቹ ወታደሮችም ቢሆኑ በዚህ ሰፍራ ሲሰነብቱ ቶሎ ነው ያገገሙት። እንደ እውነቱ ከሆነ መላው ካምፕ ዙላ ከነበረበት ሁኔታ የተለየ ነው የሆነው።


የሾሆ(ሰሆ) ጎሳ አባላት የሆኑት የአካባቢው ተወላጆች፣ ፍየሎች፣ በጎችና ላሞቻቸውን ይዘው ወደ ካምፑ ይጎርፉ ጀመር። ይህ ደግሞ አካባቢውን የዘላን ገፅታ እንዲኖረው አድርጎታል። ፍየሎቹ በአካባቢው ካለው ግራጫ መልክ ያለው ቋጥኝ ላይ በመውጣት ከበቀሉት ቁጥቋጦዎችና ተከሎች ቅጠላቅጠሉን ይቀመቅማሉ፤ ከታች፣ በጎች በሚያሳዝን ድምፅ ይጮሃሉ፤ ላሞችም [illegible] ድምፅ ያሰማሉ፤ ጠቆር ያሉና ራቁታቸውን የሆኑ የሾሆ ልጆች ደግሞ [illegible]፤ እለዚያም ከሸምበቆ በተሰራው ዋሽንታቸው ይጫወታሉ።

በአካባቢው የሚገኘው አብዛኛው ሥፍራ የገበያ ቦታ ሆኗል፤ እንደ ሱቅ የሆኑት ደግሞ መሬቱ ላይ የተዘረጉ የሰሌን ምንጣፎች ነበሩ፤ እነሱም በግራና በቀኝ ተነጥፈው በመሀሉ ለመተላለፊያ መንገድ ከፍተዋል። ሀንፃዎችና በውስጣቸው ያለው ቁሳቁስ የተለየ ባይሆን ኖሮ፣ ይህ ቦታ ከተማ ውስጥ ካለ የሱቆች ጎዳና ጋር በተወዳደረ ነበር።



የባቡር ሀዲድ በቁማይሌ
(Record of Expedition to Abyssinia)





ውሀ ማጠጫ በቁማይሌ
(ዋቢ መፅሐፍ ተ.ቁ. 16)

ገበያውን ስንመለከት፣ ብዛት ባላቸው ሸቀጦች የተሞላ መሆኑን አስተዋልን:: ሽንኩርት፣ የትምባሆ ቅጠል፣ ከስታምቡል የሚመጣ ላታኪያ ከተባለ ቦታ የሚበቅል መዓዛ ሽታ ያለው ቡናማ ቀለም ያላቸው ሥር ከምሮች የእንጨት ጠረጴዛዎች ላይ በሚያጓጓ መልኩ ተደርድረዋል፤ ቅርንጫፋቸው ላይ ያሉና በከብ ዕቃ ውስጥ የተቀመጡ የሾላ ፍሬዎች፣ ወደ አፍ ማስገቢያው በኩል ብሩህ ቀለም ያላቸው የትምባሆ ማጨሻ ቱቦዎች፣ ላያቸው ላይ የሚያምሩ ምስሎች የተቀረፁባቸው የትምባሆ ማቃጠያ መያዣዎች፣ ተራ የእንግሊዝ ከሸክላ የተሠሩ የትምባሆ ማጨሻዎች፣ ከካይሮ የመጡ የሱረት ማጨሻ ረጃጅም ቱቦዎች፣ ከፐርሽያና ከህንድ የመጡ ሁካዎች፣ ጥቁር የወይራ ፍሬ የሞሉባቸው ጠርሙሶች፣ በኪስ የሚያዙ መነፅሮች፣ የተለያዩ ፍራፍሬዎች፣ ኮኛክ፣ የሶዳ ውሀ፣ ሌሎችም ብዛት ያላቸው ከፓሪስና ከሎንደን የመጡ ነገሮች ነበሩ::

እዚህ ቦታ የማይገኙ ነገሮች ቢኖሩ በዘመቻ ለመጡት ወታደሮች የሚጠቅሙም አልነበሩም::

እንግዲህ በገፍ የነበሩ በገበያ ተፈላጊነት ያላቸው የሾላ ፍሬዎች፣ የተምር ፍሬዎች፣ አቾሎኔ፣ አረቄ ቢኖሩም እንደ መፅሐፍ፣ ፋኖስ፣ ጋዜጣ የፖስታ ቤት ዕቃዎች(እንዚህን እንኳን ያስፈልጋሉ ብዬም አስቤ አላውቅም) የመሳሰሉት ደግሞ አልነበሩም:: ገበያው፣ በሾሆ ተወላጆችና ካምፑን እየተከተሉ በሚጓዙ ሰዎች ይዘወተራል:: የአገሩ ተወላጆች የሆኑት ጠቆር ያሉት ሴቶች ደግሞ ምንም ጌጣ ጌጥ ሳያደርጉ ልብስም እንኳን ሳይደርቡ ይመጣሉ፤ ለቀቅ ያሉ ራቁት የሆኑ ልጆችም በደስታ ሲሯሯጡ ይታያሉ፤ ካምፑን ተከትለው የሚጓዙት ልብስ ደራርበው የለበሱ፣ ከበርበራ፣ ዳናኪል፣ ኤደን፣ ራቅ ካለው ከፐርሺያና ከህንድ ደናማ ቦታዎች የመጡት ወንዶች በዘረጓቸው ሱቆቻቸው ስብሰብ በማለት ሳይረበሹ በነፃነት ጋደም ብለዋል::

ቀዳሚውን ጦር ለመቅደም ጉዞዬን ማጣደፍ ስለነበረብኝ፣ አዲግራት በተባለ ጣቢያ የኮሚሳሪያቱን ክፍል ስላየሁ ሠራተኛዬን አሊን ድርሻዬን ራሽን እንዲቀበል ላኩት::

ለአንዳፍታም ቢሆን የተመደበልንን ድርሻ እንደተቀበልን ተደርጎ መታሰብ የለበትም:: የራሽን ማከፋፈያው ክፍል ሀላፊ የነበሩት ሌቦች ፋርሶች[67] ከተመደበልን ግማሹን ያስቀሩብን ነበር:: ወደ መሀል አገር እየገፋን በሄድን ቁጥር፣ በተደጋጋሚ ሩዝ፣ ሻይ፣ ስኳር፣ ቡና፣ ድንች፣ ቅጠላ ቅጠል፣

[67] Parsees (በ7ኛውና በ8ኛው ምዕተ አመት ከፋርስ (የአሁኑ ኢራን) ተሰደው ምዕራባዊ ህንድ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ናቸው::



እ[illegible]ብ አይሰጠንም ነበር:: ጭራሹን ለሁለት ወራት የሚሆን ጊዜ ከላይ የተከሰቱት ነገሮች ሳይሰጡን የከረምንበት ጊዜ ነበር::

አሊ ከኮሚሳሪያቱ ሲመለስ ፀሀይ እየገባች ነበር:: ለወትሮው ሳቂና ተሚዎች የነበረው ሰው ሀዝንተኛ መስሎ ተክዞ ነው የታየው:: እንዲህ የከፋው ምክንያቱ ምንድነው ተብሎ ሲጠየቅ በተሰባበረ እንግሊዝኛ "በገበያው ቦታ፣ አረቦቹ፣ እንግሊዞቹ በሀበሻ ምድር ይገድሉሃል ብለው ነገሩኝ። ስለዚህ ወረቀቴ ይሰጠኝና ወደ ሱዌዝ ልመለስ::" ይህን እንዳለም ሰቅ ሰቅ ብሎ ማልቀስ ጀመረ::

ነገሩ የሚመስለው፣ በእንግሊዞች ካምፕ ውስጥ በነበረው ጥብቅ ሥርአት የማስከበር ሁኔታ ያልተመቸው ቅብጥብጥ አረብ፣ አሊን፣ እንግሊዞቹ ጨካኝ ስለሆኑ ያላደላቸውን ሠራተኞቻቸውን እስኪሞቱ ድረስ ይገርፏቸዋል ብሎ ስለነገረው፣ አሊ ደግሞ በዚህ በሀበሽ ምድር ሞቶ አፅሙን ጥሎ የመሄዱ ሀሳብ በጣም ስላስፈራው፣ ወደ ሱዌዝ ለመመለስ እኔን ፈቃድ ለመጠየቅ ወሰኖ ነው የመጣው:: እኔ እሱን ያገኘሁት ሱዌዝ ነው:: ለጊዜው አፅናንቼና አረጋግቼ እንዳውም ከኔ ጋር አብረህ ሰናፌ ድረስ ትሄዳለህ በማለት አባበልኩት::

ዙላን ለቅቄ ስሄድ፣ ለራሴ የሚሆን ድንኳን ለመያዝ አልተጨነኩም፤ ምክንያቱም ሲያስፈልገኝ አገዛለሁ በማለት ነበር:: በከፊል ትክክል በከፊል ደግሞ ስህተተኛ ነበርኩ:: የራሴን በቅሎ፣ ፈረስና ድንኳን ከዙላ ብይዝ ኖሮ እንደልቤ ለመንቀሳቀስ ነፃ ነበርኩ፤ ነገር ግን ወደ መቅደላ በፍጥነት ልንገሰግስ ነው የሚባል ጭምጭምታ በካምፑ ውስጥ ሲወራ ስለነበር፣ በትክክል የማሰብ ችሎታዬን አስቀይሮኝ የባቡር ፍጥነት ያህል ተጣድፌ ለመሄድ ወሰንኩኝ:: የአየር ፀባዩ መልካም ስለነበር፣ አንድ የነበረኝን ንብረት፣ የያዝኩትን ከጎሽ ቆዳ የተሠራ ካፖርት ከብርድ ለመከላከል ስል ስለብሰው ስለነበር ብዙም ችግር በመንገድ ላይ አልተሰማኝም፤ እንዲያውም ወድጄዋለሁ::

ቀልጣፋው አሊ ያዘጋጀልኝን ቀለል ያለ እራት ከበላሁ በኋላ፣ ሲጋራ ለኮስኩና ያንኑ የጎሽ ካፖርቴን ደርቤ ተጋደምኩ፤ በአእምሮዬ ውስጥ ብዙ ስለነበረ ለማሰብ እንጂ ለመተኛትም አልነበረም::

ጎህ እንደቀደደ፣ በጊዜ፣ ኮርቻችን ላይ ወጣንና፣ የሚያዛጋ አፉን ከፍቶ ወደሚጠብቀን ማለፊያ ዘው ብለን ገባን:: ካምፑን፣ የንጋቱን ፀጥታ ከአደፈረሰው ግርግርና ጫጫታው ጋር በርቀት ወደኋላ ጥለነው ወተናል:: [illegible] መጋጠሚያዎች ዙሪያ፣ በሚሞላ ዛፎች ደኖችና ላውረል ቁጥቋጦዎች መሀል፣ ሰፋ ብሎ በተዘረጋው ቅርንጫፎቻቸው ላይ በቀለም የተንጎረጎሩ ወፎች ያሉባቸውን ከፍ ያሉ የችብሃ ዛፎችን በማለፍ እየተመራን ነበር:: የአለት ግድግዳ ያላቸው ቀጥ ያሉ ገደሎች ስር፣ ጠበብ ብለው ወጣ

ባሉት ፊትለፊት ባሉ ኮረብታዎች ዙሪያ፣ ጥቅጥቅ ባለ ደን መሀል አቋርጠው በሚሄዱ መንገዶች እየተዟዟርን መንገዳችን ቀጠልን::

ቀጥሎም፣ በማለፊያ መንገዳችን ጎንና ጎን ያሉት የጋራዎች አናቶችና ዳገቶቻቸው ምትሀታዊ በመሰለ ሁኔታ እየተቀየሩ መጡ:: ድብዝዝ ካለ ግራጫ ገፅታ ወደ ብርቱካንማ ቀለም ይቀየሩና ወዲያው ደግሞ በብርማ ቀለም ይተካሉ፤ ቀስ በቀስ ብርማ ቀለሙ በምዕራብ በኩል ያሉትን ዳገቶች ይሸፍንና ወደ ምስራቅ በኩል ባሉትም መታየት ይጀምራል:: ከላይ ከሰማያዊው ሰማይ መሀል፣ የአሳት ኳስ የመሰለች ፀሀይዋ ያለምንም ርህራሄ የእሳት ፍንጣቂ የመሰሉ ጮራዎቿን አናታችን ላይ ትለቃለች፤ አኩለ ቀን የመሆኑ ምልክት ነው:: በዚያን ጊዜም በሚሰማው ድምፅ ምክንያት የሚቀጥለው ጣቢያ ሶሮ እየተቃረብን ምምጣታችን አወቅን:: የቋጥኞቹ መጋጠሚያ ዙሪያ ወደ ቀኝ በኩል በዘጠና ዲግሪ ለንታጠፍ፣ የወታደሮቹ የካምፕ ድንኳኖች መታየት ጀመሩ::

ከፈረሴም ወረድኩና፣ ከትልቅ ዛፍ ስር፣ ጥላ ያለበት ቦታ ሳገኝ ምንጣፍ ዘርግቼ ለማረፍ ጋደም አልኩኝ:: እሊ፣ መጀመሪያ ከብቶቹን አሰማርቶ የሚያጠግብ ሳር መጠን አቀረበላቸው፤ እሳት ተቀጣጥሎ፣ ውሀ የተሞላ የቡና በራድ ቦግ ቦግ የሚሉት የእሳት ነበልባሎች ላይ ሲጣድ የቤት ትዝታን ለለሚሰብ በርካታ ፈገግ እንድል አደረገኝ፤ ከዚያ ደግሞ ሲፈላ የሚያሰማው ድምፅና ደመቅ ያለው የቡናው ሽታ ከተበታተነው ሀሳቤ አነቃኝ::

ከሁለት ሰአታት መዝናናት በኃላ እንደገና መንገዳችን በመቀጠል ወደሚቀጥለው ጣቢያ ወደ አንደል መግፋት ጀመርን::

በሶሮ ጎንና ጎን፣ ለሶስት ማይሎች የሚሆን ርዝመት የማለፊያው አስቸጋሪና አደገኛ ከፍሎች ይታያሉ:: ለስድስት ማይሎች ርዝመት ደግሞ፣ መንገደኞች በጎን በጎን እስከ 800 ሜትር ከፍታ ባላቸው ቋጥኝ ግድዳዎች መሀል ባለ ጠባብ ማለፊያ ያልፋሉ:: በነዚህ ማለቂያ የሌላቸው በሚመስሉ ግድግዳዎች መሀል፣ ድንጋዮች ላይ እየዳህን እንወጣለን፤ የረገጥነው ድንጋይ ድንገት ተፈንቅሎ እንደማይወጣ፣ ወይም የተዘረጉት የዛፍ ቅርንጫፎች ተገንጥለው ወደ ታች ወደ ማለፊያው ገደል ይዘውን እንደማይወርዱ እርግጠኛ አልነበርንም:: ዝቅ ያለ የሰዎች ድምፅ እንደነጎድጓድ ነው የሚሰማው፤ የፈረሶች ኮቴም ቢሆን ድልድይ ላይ ሲያልፍ የሚንኳኳ የመድፍ ተሽከርካሪ ድምፅ ነው የሚመስለው:: ካለንበት አስር ጫማ ከፍታ ላይ፣ በክረምት ወራት ወደ ማለፊያው ሲወረወር የነበረው የውሀ እንጥፍጣፊዎች ይታያሉ:: ሰፋ ያለው የማለፊያው መሄጃ የጎን ስፋት ሀያ አምስት ጫማ የማይበልጥ ሲሆን፣ ጠባብ ያለው ደግሞ እንደምንም አስራ አምስት ጫማ ቢሆን ነው:: አንዳንድ




ቦታዎች ላይ ወደ አገሩ ወራሪ እንዳይገባ ታይታንስ[68] ለምዕተ አመታት ቋጥኞችን ሲጠርቡና ሲያመቻቹ የኖሩበት ይመስላል:: በሺዎች የሚቆጠሩ ፏነተረሮች፣ ውሀ መውረጃዎች፣ ሥንጥቆች፣ ለሃምሳ ማይሎች ርዝመት ወደ ማለፊያው ወደ ሶሮ ሲወርዱ ማየት፣ በዚህ ስፍራ ላይ አንድ ትልቅ ውሀ ሆምንት የነበረ፣ ከዚህም ጋር ሀይለኛ አዙሪት ነበረው ብሎ መገመት ያስችላል::

በመጨረሻም፣ ከጨለማውና ድንግዝግዝ ካለው ከሶሮ ጥልቅ ሸለቆ ወጥተን ሰፋ ያለና ወደተንጣለለው የማለፊያው ክፍል ገባን:: አልፈናቸው ከመሀናቸው ቀጥ ብለው በቆሙ ገደሎች ምትክ፣ በመቶዎች የሚቆጠሩ የሚገርም ቅርፅ ያላቸው ኮረብታዎች፣ በመጠኑ ዳገታማ ከሆኑ ጎናቸውና በላያቸው ላይ በበቀሉ በቁልቋል፣ ኢጋም፣ በቁጥቋጦዎች፣ በጥድና በሌሎች ዛፎችም ተሸፍነው ይታያሉ:: ቀጥሎም፣ በጣም አስደናቂ በሆኑ ተራሮች ከፍታዎች መሀል መጓዝ ጀመርን፤ የተራሮቹ አናቶች ደግሞ በትንንሽ ሾጥ ሾጥ ባሉ ድብዝዝ ያሉ አለቶች የተቆራረጡ ናቸው፤ ይህም በማለፊያው ከታች ወይም ስሩ ላይ ትልልቅ ጥርብ አለቶች በአፈር አልፎ አልፎ ተሸፍነው ተጋድመው የሚታዩበት ቦታ እስከንደርስ ነበር:: እነዚህ ጥርብ አለቶች ሆን ተብለው ከላይ ቁልቁል የተወረወሩ ይመስላሉ:: አልፎ አልፎ ሾለክ ብሎ የሚወርደው የፀሀይ ጨረር ሲያርፈባቸው እንደ አልማዝ የሚያንፀባርቁ የነዚህ ግዙፍ ጥርብ አለቶች ከፍሎች አይን ይሠርቃሉ:: እንደገናም፣ አይን፣ ከላይ ሾል ሾል ብለው ወደቆሙት፣ የተራራው አናት ላይ የሚገኙ ከንፁህ ሰማያዊው ሰማይ ጋር የሚነፃፀሩትኝ የአለት ከፍሎች ያማትራል::

ደማቅ ፀሀይ በርቃ፣ የተራሮቹን አናቶች ብርሃን ስታፈስበትና፣ ኮረብታዎችን የቀለተ ደመና ህብር በመሰለ ቀለም ስትኩላቸው፣ የእንኳን ደህና መሀከሉ የካምፕ እሳት ወደ ሚታይበት አንደል ዌልስ ካምፕ ደረስን፤ ለዚያን ቀን ላደረግነው ድርብ ጉዞ ማቆሚያ ቦታችን ነበር::

ሌላ የሙሉ ቀን ረዥምም ጉዞ፣ ከዚህ ቀደም እንደተገለፁት አይነት ቦታዎችን በማለፍ፣ ከትልቅ ቀጥ ብሎ ከቆመ ተራራ ስር አደረስን፤ የወታደሮቹ መንገድ፣ መጠነኛ የሆነ ዳገታማ ቦታ እስኪደርስ ድረስ በዚህ ጋራ ዙርያውን ተጠምጥሞ ነበር የሚሄደው:: በዚህ ዳገታማ ጋራ ለግማሽ ማይል የሚሆን ወደላይ ሌላ ከፍተኛ ዳገት ከወጣን በኃላ፣ በመጨረሻ፣ ከባህር ወለል በላይ ስምንት ሺ ጫማ ከፍታ ላይ የሚገኝ የአቢሲኒያ ደልዳላ ቦታ ደረስን:: ይህ

[68] ታይታንስ (Titans ) ግዙፍ ጃይንቶች ወይም ከሰው ተፈጥሮ በላይ የሆኑ



የሶሮ ማለፊያ (የዲያብሎስ ደረጃ) *Record of the Expedition...*



ቦታ ሥዕሉ ሰፋ ያለ እይታ አለው፡፡ በመጀመሪያ እይታ ብቻ፣ ትልቅ ሜዳማ የሆነ ቦታ፣ እዚህም እዚያም ገደሎች እንደ ነጠብጣብ ይታያሉ፤ ብዛት ያላቸው የማያቋርጡና ቅጥ የሌላቸው ጉድጓዶች መሬቱን በሰተውት የማር ሰፈፍ አስመስለውታል፤ ከዚህ በተጨማሪ ሰፋፊ ሰንጥቆችና በእሳተ ገሞራ አማካኝነት የተቆራረጡ የመሰሉ፣ አይን የማይሰቡ የጋራ አናቶችም ይታያሉ፡፡ ከዛ ብለው ከቆሙት፣ ከትልቁ፣ ግራጫ መልክ ያለው ቀጥ ብሎ ተኮሳትሮ የቆመ ቋጥኝ ስር ሰናፌ ይገኛል፡፡ ከደጋማው ከፍታዎች ጠርዝ አንድ ማይል ርቀት ላይ ነው ያለው፤ ይህ እንግዲህ፣ ጠቀሜታ ያለው የአቢሲኒያ መንደር ሰናፌ የመጀመሪያው ነው፡፡ ከመንደሩ ፊት ለፊት፣ በመቶዎች የሚቆጠሩ ያርዶች ርቀት፣ ከትልቅ ግራጫ መልክ ባለው ቋጥኝ ጥላ ስርና ትንሽ ጉብታ ላይ የተዳሚው ጦር ካምፕ ይታያል፡፡ ከጉብታው ጀርባ፣ በመሬት የታጠረ፣ በየትም አቅጣጫ የሚመጣን ሀይል ለመቆጣጠር በሚመች ቦታ ላይ የትጥቅና ስንቅ ክፍሉ የሰፈረበትና በቅሎዎች የታሠሩበት ቦታ ነው፡፡ አልፎ አልፎ በተዘረጋው ቦታ ላይ ማዕረግ ያላቸው ሰዎችና ዕድሉ የተሠጣቸው የጦር መኮንኖች ድንኳኖች ተተክለዋል፤ ባለ ድንኳኖቹ ደግሞ፣ እንግሊዞችን በተለይ የሚያስደስታቸውን ቀዝቃዛውንና ነፋሻውን አየር ለመቀበል የታደሉ መሆናቸው ነው፡፡

ከነጫጭቹ ድንኳኖች በቂ ርቀት፣ የፍየል መንጋና ጅራተ ሰፊ በጎች፣ ጀርባቸው ላይ የበግ ቆዳ ጣል ባደረጉ ልጆች ይጠበቃሉ፤ ልጆቹ፣ ከርቀት ቀይ ዩኒፎርም የለበሱትን የእንግሊዝ ወታደሮች፣ የሚያብረቀርቁ ጠመንጃዎችንና የሚቀነጠነጡትን የወታደሮችን ፈረሶች በአድናቆት ይመለከታሉ፡፡

እንደለማሁት ከሆነ ሰናፌ በማታ በጣም ይበርዳል፡፡ ድንኳን ለማግኘት ማመልከት እንዳለብኝ ወሰንኩ፤ በዚህ መልካም ሀሳቤ ተማምኜ፣ በመሀል ካምፑ ውስጥ ወደ ተተከለው የዋናው አዛዥ የተንጣለለ ድንኳን ርምጃ ጀመርኩ፡፡ ዋናው አዛዥ፣ ጄኔራል ኤም ይባላል፡፡ ባጭሩ፣ ከሱ ጋር ያደረግሁት ቃል ልውውጥ፣ "ደህና አደር" በሚል ቃል ቢጠቃለል ይሻላል፤ በተጨማሪም የተሠጠኝ ማረጋገጫ፣ ሁለተኛ የሱ ድንኳን ውስጥ ብገኝ እርሱ ራሱ እንድመጣ ልኮብኝ ከሆነ ብቻ ነው፡፡ እየጋለብኩ ከጄኔራሉ ድንኳን ርቄ ስሄድ፣ በውስጤ ለእንግሊዞች ምንም አይነት የፍቅር ስሜት እንደሌለኝ እየተሰማኝ ነበር ድንገት በሥርአት በለበሰ መኮንን፣ ሰው እየፈለግሁ እንደሆነ ስጠየቅ፡፡

"የለም፣ ማንም የምፈልገው ሰው የለም፡፡" አልኩኝ እየሳቅሁኝ፣ "ማታ የማድርበት መኝታ ቤት እየፈለግኩ ነው፡፡"



*በቁማይሌ ማለፊያ ፣ አንደል ዌልስ*
(ዋቢ. መፅሐት ተ.ቁ. 16)



"መንታ ቤት! የኔ ጌታ፣ ሰናፌ ውስጥ እንደልብ አይገኝም፤ ነገር ግን፣ እናንተን ለማስተናገድ ደስተኛ የሚሆኑ ብዙ ደግ ሰዎች አሉ።"

"እህ፣ አምንሀለሁ ጌታው፤ በርግጥ፣ ግን የምታውቀው ስም ልትነግረኝ ትችላለህ?"

"እንዴ፣ አዎ፣ ካፒቴን ስመልፈንገስ የሚባል አለ።" (የስተርንን "ትዝታ ያለው ጉዞ" የሚባለውን ያነበቡ አንባቢዎች ይህንን ስም አይረሱም)"ትልቅ ዝናን አለው፤ እሱ..."

"ምን!" አልኩኝ፣ "ስመ ጥሩው ካፒቴን ስመልፈንገስ እዚህ አለ? ስለዚህ ትልቅ ሰው በየቦታው ነው የሰማሁት። መጀመሪያ በእስክንድሪያ፣ ከዛ በሱዋኪን፣ ዙላ፣ ቁማይሌ፣ እና አሁን ደግሞ ሰናፌ ብቅ አለ። ወደ ድንኳኑ ሊያመላክተኝ ትችላለህ? በጣም የሚያስገርም ሰው ስለሆነ፣ አሁኑኑ እንግሊዛዊው እያለ መተዋወቅ እፈልጋለሁ።"

"እህ፣ በሚገባ፣ ትንሽዋ ዳገት ላይ ብቻውን ያለ ድንኳን ይታይሃል? ካፒቴኑን እዛው ታገኘዋለህ። እንደማይህ ከሆነ የተጣደፍክ ትመስላለህ፣ ሰላም እደር።"

"ደህና እደር፣ በጣም አመሰግንሃለሁ፣" ከልቤ ነበር የመለስኩለት። ከዛም ፈረሴን ኮልኩዬ ከካፒቴኑ ድንኳን ፊት ደረስኩ።

ከካምፑ አቅጣጫ በቁልቁለቱ፣ አጠር ችፍግ ያለ ፂም ያለው ሰው በፈረስ ሲመጣ አየሁ፤ ሰውዬው ቡናማ ቀለም ያለው ልብስ ለብሷል፤ ጠመንጃው ከወገቻው ጎን ባለ አፎት ውስጥ ይታያል፤ ሁለት ያደናቸውን የወንዝ አሞራዎች ለማሳየት ይመስል በእጁ እያወዛወዘ ነው፤ አደን ለመውጣቱ መረጃም ነው። ከፈረሱ ወርዶ፣ ፈረሱንና የያዛቸውን ሁለት አሞራዎች ሲረዱት ለመጡት ሁለት አገልጋዮች ከሰጠ በኋላ ዞር ብሎ ሲመለከት አንግዳ መልኩን ለመጀመሪያ ጊዜ ይገነዘባል። ከትልቅ ፈገግታና ከይቅርታ ጥያቄ በኋላ፣ ይህ ግሩምና ታላቅ ሰው፣ በምን መንገድ ሊረዳኝ እንደሚችል ጠየቀኝ።

"የመጣሁት ካፒቴን ስመልፈንገስን ፈልጌ ነው፣ ጌታው፣" አልኩኝ፤ "ባልሳሳት፣ ሰውዬው አንተ መሰልከኝ።"

ወፍራሙን ፂሙን፣ ደኅስ ባሉ ጣቶቹ እያሻሸ፣ እንደገናም በሰፊ ፈገግታ ፊቱን ፈካ አድርጎ፣ "አዎ ጌታው፣ ሰውዬው እኔ ነኝ።" አለ።

እኔም ፂም የለሽ ፊቴን በመዳፌ እየዳሰስኩ፣ ቀደም ሲል የተሰማኝን የነበረኝ ስሜት በማስለስ መልክ እሱ እንዳደረገው ሁሉ እገጩን እሸት እያደረግሁ፣ ስለሱ፣ ስለችሎታው፣ የተለየ ሰው የማሳብ ችሎታውና ስለ

ተቀዳጀው ድሎቹ ብዙ የለማሁ ስለሆነ ሳላገኘውና ሳልተዋወቅ ማደሩን አልፈለግሁም ብዬ ነገርኩት፡፡

"አሀ፣ ጌታው፣ ከሚገባው በላይ ክብር ሰጠኸኝ፤ ለመሆኑ ለመነጋገር ይህን አስደሳች አጋጣሚ ያገኘሁት ከማን ጋር ነው?"

የሚፈልገውን አስደሳች አጋጣሚ ያለ ምንም ገደብ ነው የሰጠሁት፡፡ አሜሪካዊ መሆኔን ሰናገር፣ ጆሮዎቹ ቆሙ፤ አይኖቹን ወደላይ አንከባለለ እናም ፂሙን እንደማይሆን ሊያደርገው ነበር፤ ነገር ግን ጋዜጠኛ መሆኔን ሰጠቁም፣ በርግጥም እንዲህ አይነት የተቀደሰ የመሰለ ስሜት በፊቱ በሚታይ ምልክት ይገለፃል ብዬ አልገመትኩም፤ በስሜት ስለተሞላም፣ ሲናገር ቃላቶች ጎሮሮው ላይ ተሰንቅረው የቀሩ ይመስል ነበር፡፡

ሲናገርም፣ ያገሩ ልጅ እንደሆንኩ፣ ወንድሙ ማለትም እንደሆንኩ፣ በዜግነት ብቻ ሳይሆን በሙያ ጭምር መሆኑንም ገለፀ፡፡ ድንኳኑ የኔ እንደሆነ፣ ሰራተኞቹም፣ ያለው ራሽንና ማብሰያ ቁሳቁሶቹ የኔም እንደሆነ አረጋገጠልኝ፡፡ እንድ ጋዜጠኛ ከዚህ በላይ ምን ይመኛል? እዚህ ቦታ፣ እንግዲህ፣ ቤት፣ ሠራተኞች፣ በቂ የማብሰያ ቁሳቁሶች፣ የተትረፈረፈ ራሽን ከዚህም በላይ የተከበረ ያገሬ ልጅና ወንድም ተገኘ፡፡

"ጓደኛ፣ አሁን ግን ወደ ውስጥ፣ ወደ ሽራው መኖሪያዬ እንግባ፡፡ ለእንግዳም የሚበቃ፣ ለፈጣሪ የሚሆን እራት ተዘጋጅቶ እየጠበቀን፣ ለምን በዚህ ምሽት ውጭ እንቆማለን፡፡" ምስጋና የተሞላበት እንግዳ ተቀባይ የሆነ ንግግሩን ከጨረሰ በኃላ፣ እኔና አዲሱ ጓደኛዬ ወደ ድንኳኑ ገባን፡፡ በውነትም የሚያጓጓ ምግብ ተዘጋጅቷል፡፡ በዚህ እንዳለን፣ የኔው ውዱ አሊ ሁለቱን እንስሶች ይዞ ደረሰ፤ ጭነታቸው ወረደላቸውና ከካፒቴኑ የከብቶቹ ምግብ እንዲመገቡ ተደረገ፡፡

አንድ ነገር መናገር አለብኝ በሚል፣ ያለምንም ስሜታዊ ንግግር፣

"ይቅርታ አድርግልኝ ካፒቴን፤ ባልሳሳት፣ ከጋዜጣ ጋር ግንኙነት እንዳለህ ነካ አድርገህልኝ ነበር፡፡" አልኩኝ፡፡

ካፒቴን ሰመልፈንገለ፣ እንዴት ብሎ በጣም ከፍተኛ የሆነ ታዋቂ የጋዜጣ ሰው እንደሆነ አድርገው ሌሎች እንዲያዩት እንዳደረገ፤ ወይም እንዴት ብሎ በእንግሊዞች ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ከፍተኛ ሥራ እንደተመደበ ለመግለፅ መብቱ ወይም ፈቃድ የለኝም፡፡ ግን ከዛ ቀን ጀምሮ የሰመልፈንገለ የምግብ ጓደኛ ነው የሆንኩት፡፡

በነገታው ጠዋት ሰነሳ፣ ፀሀይዋ መሀል ሰማዩ ላይ ከፍ ብላለች፡፡ ጎበዙ ካፒቴን፣ በላዩ ላይ "ሰር X. Y." የሚል ፅሁፍ ካለበት ከአንድ ረዥም ሳጥን እጠገብ በርከክ ብሎ፣ አንድ ትልቅ ሰው ሊኖረው የሚገባው በውስጡ ያሉትን



ነገሮች ያገላብጣል፡፡ ቀጥሎም፣ በወርቅና በብር የተሰሩ ኮከቦችን፣ ሜዳሊያዎችን በጥንቃቄ ያስቀምጣል፡፡ እንደገናም፣ ከህንድ የፑቲያላ መሀራጃ የተሰጠውን ለየት ያለ የጨቤ ሰጦታ አላየኝ፤ በሀይደራባዱ ኒዛም የተሠጠውን ሰይፉ፣ የተለየ ያጌጠ ከዘራ፣ ከባሮዳው ጉዊኮዋር፣ ብጫማ ቀለም ያለው የእንስት ሁብል ከቦፓል ቤገም፣ ከካምብሪጅ መስፍን የተሠጠው ጎራዴ፣ ከጀነራል ቤኔዲክ፣ ከኮኒገራትዝ ጦርነት ከሁለት ቀናት በኃላ የተሠጠው እፊ መዝገቡው ሰፋ ያለ የዱዌል ሽጉጦች፣ ከአሜሪካው ጀኔራል ሮበርት ኢ ሊ[69] የመለያየ ሰጦታ ከብር የተሠራ ሪቮልቨር ኮልት ሽጉጥ፣ እና ሌሎችም ቁጥራቸው በርከት ያሉ ነገሮች ነበሩ፡፡

"ሣጥኑን እንደገና እየት አደረግሁና፣ "ከሰር X. Y. ጋራ ዝምድና አላችሁ?" ብዬ ጠየቅሁት፡፡

"እዎ፣ የወንድሜ ልጅ ነው፤ በቅርብ ጊዜ ሲሞት፣ በዶረሰትሻየር የሚገኝ ዋጋው 7ሺ ፓውንድ የሚሆን ምን የመሰለ ቤት ለኔ በውርስ ተወልኝ፡፡"

"አሀ፣ በርግጥ! በጣም ጥሩ ንብረት ነው፡፡ እንዳንተ ያለ፣ ከብዙ ሰው ጋር ትውውቅ ያለው ሰው እንዲህ አይነት ጥሩ ንብረት ይጥልለታል፡፡"

"እዎ፣ ልክ ነው፡፡" አለ፡፡ ቀጥሎም በአልባሌ አነጋገር፣ "ለነገሩ እንኳን ግማሽ ዶዘን የሚሆኑ የዚህ አይነት ትንንሽ ቤቶች በተለያዩ የእንግሊዝ አገር በታዎች አሉኝ፡፡"

እኔም፣ ወደ ጦር ግንባሩ መቼ ለመሄድ እንደወሰነ ጠየቅሁት፡፡

"ያለ ምንም ጥርጥር፣ ዛሬ ማታ፣" ብሎ መለሰ፡፡

"እንደሱ ከሆኔ ለኔም ይመቸኛል፤ ለፈጣን ጉዞ በአንደኛ ደረጃ ዝግጁ ነኝ፡፡"

"እንደተዘጋጀህ እያለሁ፤" አለ በፈገግታ፡፡ "ነገር ግን፣ ብዙ ዕቃዎች ነው ያሉኝ፣ አምስት የጭነት ከብቶች ያለኝን ዕቃ በሙሉ መጫን መቻላቸውን እጠራጠራለሁ፤ ያው የተለመደ የመንገደኞች አባባል እንደሚለው መውሰድ የማይችሉትን ዕቃ ጥሎ መሄድ ነው፡፡"

ካፒቴን ሰመልፈንገለ ለካምፕ የሚያስፈልጉ ማንኛውንም ቁሳቁሶች በሚገባ ይዟል፡፡ ትልቅ የአሜሪካ ድንኳን፣ አነስ ያለ ድንኳን፣ ቁጥር ያላቸው የዝምባ ጀበናዎች፣ ሰሀኖች አሉት፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የሚበቃ የተለያዩ የምግብ አይነቶች ከአምስት ሠራተኞች ጋር አለው፡፡

ቀኑን ሙሉ፣ ካፒቴኑ ከጓዙ ጋር ሲባትል ነው የዋለው፡፡ ያለምንም ሰራት ከአንዱ ወዳንዱ ሲሯሯጥ፣ አንዴ ፈረሶቹን፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ

[69] ጀነራል ሮበርት ኢ ሊ(በተጨማሪ ማስታወሻዎች ምዕራፍ ይመልከቱ)፡

የሚሰናዳውን ጓዝ፣ የሚሄደውን ሲያዘጋጅ፣ የማይጠቅም የመሰለውን ሲወረውር፣ እንግዲህ እሱ ለመንገድ ሲዘጋጅ፣ ዙሪያውን አሰፍስፈው የሚመሰከቱ የአቢሰኒያ ልጆችም አሉ፤ እነሱም መንገደኛው አይረባም ብሎ የሚጥለውን ዕቃ አፈፍ ለማድረግ ተዘጋጅተው ይጠብቃሉ።

ከፀሀይ ግባት አንድ ሰአት በኃላ ነው ሁሉም ነገር ተጠናቆ መንገዳችን የጀመርነው። ከማሰፈያው ሰሮ አጠገብ ካለ ከፍታ ላይ ሆኖ የሚታይ አስገራሚ ዕይታ አለ ሲባል ስለሰማሁ ለማየት ወደ ተባለው ቦታ አመራሁ።

በከፍታው ቦታ፣ ጫፍ ላይ ከወጣሁ በኋላ እራሴን ለሚታየው ዕይታ አዘጋጀሁኝ፤ ወደ ምስራቅ አቅጣጫም ተመለከትኩ፣ በርግጥም ሠአሊ ሰሎት የማያውቀው አስገራሚ ዕይታ ነበር።

ይህንን ቦታ ያዩ ሰዎች ለአድሜ ልክ የሚረሱት ነገር አይደለም። በዚያ በአንድ ቅፅበት፣ እየሸሸ የሚሄደው፣ የሚበርቅ የፀሀይ ጮራ የአድዋ ተራሮች ላይ አብርቶ፣ ማቆሚያ የሌላቸው የሚመስሉትን የተራራ ሰንሰለቶች በብርሃን ባህር ያጥለቀልቃቸዋል፤ ይህም ፀሀይ አስከትጠልቅና ሌሎች ከተራሮቹ ጀርባ ያሉትን የአሰም ከፍሎች አስከታበራ ድረስ ነበር።

## የምዕራፍ ሁለት ማስታወሻዎች

*__ቁጥር 61፤__ ይህን ደሴት፣ ደጃች (አገው) ንጉሴ ለፈረንሳዮች በሥጦታ ስለሰጣቸው ለተወሰነ ጊዜ ይዘውት ነበር፤ ሆኖም በምፅዋ የነበሩት ቱርኮች በታውን እንዲለቁ ሊደርጋዋቸዋል። ደጃዝማች ንጉሤ ወልደ ሚካኤል የደጃች ውቤ የእህት ልጅ ነበር። ቴዎድሮስ ደጃች ውቤን ቧሂት ላይ ድል ሲያደርጉ ደጃች ንጉሤ ቆስሎ ስለነበር፣ ቴዎድሮስ፣ ማር፣ ቅቤ፣ ፍሪዳ ሰጥተው "እድኑት" ብለው ሄዱ። ንጉሤም፣ ሲድን ሸፍቶ፣ ብዙ ጭፍራ አሰከትሎ ብዙ ጉዳትም አድርሶ ነበር። ፈረንሳዮች ከሮማ ካቶሊኮች ጋር በመተባበር የንጉሤ ደጋፊዎች ከመሆናቸው በተጨማሪ፣ የፈረንሳይ መንግሥት፣ ንጉሤን የአቢሲኒያ ንጉሥ በማለት ዕውቅና ሰጥቶት ነበር። ለዚህም ነው ደሴቱን በሥጦታ የሰጠው። የቴዎድሮስ የወንድም ልጅ ጋረድ ከንፋ ሲሸፍት ከንጉሤ ጋር አብሮ ነበር። አፄ ቴዎድሮስ፣ ትግራይ ድረስ በመዝለቅ፣ አክሱም አጠገብ ሳጋሞ የሚባል ቦታ ከንጉሤ ጋር ይፋጠጣሉ። የሚባለው፣ ሌሊቱን ወደ ንጉሤ ካምፕ መልክተኛ ተልኮ፣ ንጉሤን ከድቶ ለሄደ ወታደር በሙሉ ምህረት ይሠጣል የሚል መልክት ይሠራጫል። ንጉሤና ወንድሙ ተሰማ፣ በጠዋት ሲነሱ ሠራዊታቸው ከድቶ ለቃሊ ሃገራቸውን ሆነዋል፤ ከዛም ወደተንቤን ሸሽተው ነበር። ግን ከተያዙ በኋላ በፍትህነገሥቱ መሠረት በሞት ተቀጥተዋል። የቋመጡት ፈረንሳዮችም መሬት ሳያገኙ ቀሩ። ቴዎድሮስ ንጉሤን ድል ከመቱ በኋላ፣ ትግራይ ላይ፣ ትክክለኛውን ወራሽ፣ የነቢጉዲስን ልጅ ካሳን (ካሳ ምርጫን አይደለም) ሾመው ተመልሰዋል። በዚያን ጊዜ መልከኛ የነበረቸው፣ የካሳ ሰባጋዲስ ልጅ፣ አበራሽ፣ ባሏ፣ ተሰፋጽዮን የሚባል የሐማሴኑ ገዥ የደጃች ሃይሉ ልጅ፣ በንጉሤ ተገድሎ ባል አልባ ነበረች። አቴጌ ተዋበች ከሞተች በኋላ ስለነበር፣ ቴዎድሮስ አበራሽን እንደ ዕቁባት ወስደዋት ነበር። በዚህም ከትግራይ ጋር የነበረው ግንኙነት ለማጠናከር ነበር። ሆኖም አበራሽም ሆነ ሁሉ፣ ካሳ ሰባጋዲስ፣ ብዙም ሳይቆዩ ሁለቱም ሞቱ።*

*በዚያን ጊዜ ፈረንሳዮች፣ በኢትዮጵያ ወሰን፣ ቀይ ባህር ደንበር ቅኝ ግዛት ቦታ ለመመስረት ይፈልጉ ነበር። በህዳር ወር፣ ካውንት ደ ቢሶን የሚባል የፈረንሳይ ጄኔራል ከብዙ ተከታዮች ጋር ሐማሴንን ለመያዝ መንቀሳቀሱ ሲሰማ፣ የሐማሴን ባላባቶች ሰውዬውን ለመውጋት ጦር አደራጅተው ከዚያም ለአፄ ቴዎድሮስ ስለ ፈረንሳዮች እንቅስቃሴ መልክት ልከዋል። ይህ ደግሞ፣ ቴዎድሮስ በአውሮፓውያኑ ላይ የነበራቸውን ጥርጣሬ አጠናክሮታል። ይህ የፈረንሳይ ጄኔራል፣ ከአስራ አምስት ሠራት በፊት በግብፅና በሌሎች ቦታዎች የሰበሰባቸውን 40 የሚሆኑ ሰዎች ይዞ ወደሐማሴን መጥቶ ቅኝ ግዛት ለመመስረት ሞክሮ ነበር፤ ሆኖም በሐማሴን ተወላጆች ከፍተኛ ተቃውሞ ስላጋጠመው፣ ያመጣቸውን ሰዎች በትኖ ተመልሷል።*

*__ቁጥር 62፤__ ኮሎኔል መርዌዘር፣ አፄ ቴዎድሮስ የጠየቋቸውን መሳሪያና ቁሳቁሶች በሙሉ ወደ ኢትዮጵያ ለመምጣት ተዘጋጅቶ ነበር ግን በእንግሊዞቹ ፍራቻ ማለትም*

*እነዚህስ ቢታሰሩስ በማለት፤ በተጨማሪም እነስተርንና ካሜሩን ከውስጥ ሆነው በስውር በሚልኳቸው ደብደቤዎች ጉዳዩን በመቃወም ነው የቀረው:: ሰውየው ሊያመጣቸው የነበሩ ቁሳቁሶችና የሠራተኞች ክፍያ ተደምሮ፣ 3500 የብሪታንያ ፓውንዶች ነበር የሚያወጣው:: ቴዎድሮስ ይህን ቢያገኙ ሰዎችን ይለቁ ነበርን? የሚ ጥያቄ ነው:: ሌላው ደግሞ፣ ራሳም ራሱ፣ 500 ጠመንጃዎች ለቴዎድሮስ በሥጦታ መልክ እንዲሰጥ ተሰጥቶት ነበር:: ሆኖም፣ ጉቦ ነው ብለው ቴዎድሮስ እንዳይናደዱ፣ በተጨማሪ በየመንገዱ ያሉ ሽፍቶች ወይም የቴዎድሮስ ተቃዋሚዎች ንጉሡን ረዳችሁ ብለው ይጣሉናል በማለት ሳይወስድ እንደቀረ ያትታል:: መንገድ ላይ በነበሩ ሽፍቶች ምክንያት፣ በዚያን ጊዜም እናም ቀደም ብሎም ብዙ የውጭ ሰዎች በሱዳን አልፈው፣ በምዕራብ፣ በመተማ በኩል ነበር ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡት:: ከመተማ ወደ መሀል ከመግባታቸው በፊት፣ በጭልጋው ገዥ በባላምባራስ ገልም በኩል ማለፍ ነበረባቸው:: በዚህ በኩል ከገቡት አንዱ፣ ሄንሪ ዱፈተን፣ ስለ መንገዱ በዝርዝር ዘግቧል:: ዱፍተን የገባው ከፈረንሳዊው ሌዣን ጋር ነበረ:: ቴዎድሮስ እህያ አየጋለበ መጣ ብለው ከንቀት በመቁጠር በሌዣን ቢናደዱም፣ በእህያ ጀርባ የገባው ግን ዱፍተን ነበር::*

***ቁጥር 66፤*** *እንግሊዞች፣ በዚህ ማለፊያ፣ በግራኝ መሐመድና በፖርቱጋል ወታደሮች መሀከል የተደረገውን ውጊያ አጥንተው ስለነበር፣ ማለፊያው በክረምት ሆነ በበጋ ሊታለፍ ይችላል የሚል ግምት ነበራቸው:: በዚህ ሥፍራ ነበር የፖርቱጋል ወታደሮች መሪ የነበረው ክርስቶፎር ዳጋማ የተገደለው:: ፅሁፎች የሚጠቅሱት፣ ግራኝ አህመድ የሰውየውን ጭንቅላት ቆርጦ ወደ ምፅዋ በመላኩ፣ የቱርክ ወታደሮች ሳይቀር ተናደው ግራኝ ጥለው ተመልሰዋል::*

***ቁጥር 69፤*** *ጄኔራል ሮበርት ኢ. ሊ፣ በአሜሪካ የእርስ በርስ ጦርነት፣ የደቡብ ወይም የኮንፌደሬት ሠራዊት አዛዥ ነበር:: ጄኔራሉ በኮሎኔልነት ማዕረግ እያለ፣ ታዋቂ የፀረ ባርነት እንቅስቃሴ(Abolitionist) ባለታሪኩን፣ አሜሪካዊው ጆን ብራውን፣ በቨርጂኒያ በጦር መካዝን ላይ ጥቃት ሲያደርስ የማረከ ሰው ነው:: ጆን ብራውን በስቅላት ቢቀጣም፣ በደቡብና በሰሜኑ መሀከል ለተከሰተው የርስ በርስ ጦርነት መቀጣጠል አንዱና ትልቁ ምክንያት ነበር:: ሰውየው ነጭ ነበር፣ በአሜሪካው ፕሬዚደንት፣ የአሜሪካ የፖስታ ቤት ሀላፊ ሆኖ ተሹሞ ነበር:: ነገር ግን የባርነት ሥርአቱን ለመገርሰስ የትጥቅ ትግል ጀመረ:: በመጨረሻው ዘመቻ፣ ሁለቱ ልጆቹ በግጭቱ ተገድለዋል:: በዚህ ጊዜም፣ አፄ ቴዎድሮስ በኢትዮጵያ የሚባትሉበትና የባርነት ሥርአት እንዲጠፋ የሚታገሉበት ጊዜ ነበር:: የሮበርት ኢ. ሊ ሀውልት እንዳይፈርስ ለተቃውሞ በተሰለፉ እፍቃሪ ናዚና ነጭ አክራሪዎችና በነሱ ተቀዋሚዎች መሀከል በተደረገው ግጭት፣ ቻርሎተስቪል በሚባል በቨርጂኒያ ከተማ የአንድ ሰው ህይወት አልፏል:: ነሐሴ 2017.*

# ምዕራፍ ሶስት

## አስገራሚ የማታ ጉዞ፣ የአቢሲኒያ ሸንጎ፣ የተወሳጆች ዲስኩር

የጨለማ ጉዞ፣ ሰውን የሚያጓጓ ምንም ባህሪ የለውም:: መንገደኛው በዙሪያው ያለውን ፅልመት አሻግሮ ለማየትና ክፍተት ቦታ ለማግኘት ያለመታከት ይጥራል::

በዚህ በመጀመሪያው ወደ አቢሲኒያ ዋና ምድር የጨለማ ጉዟችን፣ ሀሳባችንና ምኞታችን ሁሉንም ነገር ቢያካትትም ተስማሚ ግን አልነበረም:: ጨለምለም ማለት ጀምሮ ነበር፤ ገና አንድ ሰአት የሚሆን መንገድ እንኳን አልተጓዝንም፣ የዱር አውሬ መንጋ እየተከተለን ነው ብለን ማሰብ ስንጀምር:: የኮቴ ድምፅ የሚያሰሙና፣ ልዕለ ተፈጥሯዊ በሆነ ቅፅበታዊ ፍጥነት አልፈውን የሚያደርሱብን ነው የመሰለን:: ወዲያው ግን፣ ፀጥ ያለውን ጨለማ ያደፈረሰ የሚያስካካ ድምፅ በዙሪያችን እየተቀባበለ መስማት ጀመርን:: ወዲያው ደግሞ ሌላ ፍፁም ፀጥታ ተከተለ፤ ነገር ግን ወዲያውኑ አስፈሪ የአውሬ ድምፅ ተከተሎ መጣ፤ ያሁኑ እንኳን ወደኛ ቀረብ ያለ ነበር:: ሳናስበው በድንገት ሩጫ ጀመርን:: ከዚህ ቀደም የአንበሳ፣ የነብር ወይም የአነር ድምፅ ደጋግሜ ሰምቼ፣ አውቃለሁ፤ ግን እርግጠኛ ነኝ፤ ይህ የሰማሁት ድምፅ የአንደኛቸውም አልነበረም፤ አብሮኝ ያለው ካፒቴን የመንገድ ልምድ ያለው ነው ብዬ በማሰብ ጥያቄዬን አቀረብኩለት:: ካፒቴኑ፣ የአውሬውን ጩኸት ከመስማታችን በፊት ከኛ ቀደም ብሎ ነበር የሚጓዘው፤ ለተከታዮቹ ወታደሮች መንገድ እንደሚመራ ሰው፣ በእጁ ትልቅ ጦር ይዟል፤ አያያዙም ትክክለኛ የተዋጊ አይነት ነበር፤ ነገር ግን፣ ቀስ እያለ ፍጥነቱን በመቀነስ አሁን ከኔ ጎን ለጎን ይሄዳል::

"ምን አይነት አውሬ ነው? ካፒቴን" ይህን እንደጠየቅሁ፣ በራሴ ድምፅ የተበረታታሁ ይመስል፣ ድንገት ወዳለሁበት ሁኔታ አእምሮዬ ሉብሰብ ማለት ጀመረ::

"ጅብ ነው፣" በማለት ሰውየው መልስ ሰጠ::

"አደገኛ አውሬ ነው ወይ ? "

"በጣም"፣ ነበር ምላሹ

"ይተናኮለን ይሆን?"

"እኛ ካልተናኮልነው በስተቀር አይነካንም::"

"ግን በያዝከው ጦር ብትፈታተነውስ?"

"የለም፣ አመሰግናለሁ።" በማለት መለሰለኝና ሲቀጥልም፣ "ለሱ ስል ጦሬን አላበላሽም። ይልቁንስ ለአንበሳ፣ ጎሬላ፣ ለጉማሬ ወይም ለዱር አሳማ ብጠቀምበት ይሻላል።"

ከዚያ በኋላ አልጨቀጨቅኩትም። የሱ እጠገቤ መሆን ብርታት እንደሰጠኝ ያሰበ መሰለኝ፤ እናም ከአራት ሰአታት በኋላ ጉና ጉና እስከንደርስ ድረስ ከጎኔ አልተለየኝም።

የጅቦቹና የተኩላዎች ድምፅ ሌሊቱን በሙሉ ከአጠገባችን አልራቀም፤ ወይ እየተከተሉን ነበር፤ አለዚያም አጠገባችን በብዛት ነበሩ ማለት ነው።

ጉና ጉና ካምፕ አካባቢ የእውሬዎቹ ጩኸት በጣም ደመቀ፤ ስህገሩ እንግዳ ስለነበርን ካፒቴኑ ለኛ በማሰብ ድንኳናችን በካምፑ መሀል እንድንወጥር አደረገን፤ ይህም ከዱር እውሬዎች ጥቃት በደንብ ይጠብቀናል።

ከመተኛታችን በፊት ግን፣ በመሀል አቢሲኒያ አየሩ ቀዝቃዛ ስለነበር ደመቅ ብሎ በሚነድ እሳት ዙሪያ ተሰባሰብን። ይህንን እሳት ያዩ የካምፑ ወታደሮችም፣ አዲስ የመጣነውን መንገደኞችን በዛው ሰላምታ ለመስጠት ሲሉ ተቀላቀሉን። ከሁሉም በላይ፣ በለበሰው ቡናማ ቀለም ያለው ልብሱ፣ ኮራ በማለቱና በማዕረጉ ምክንያት፣ የአብዛኛውን ትኩረት ያገኘው ካፒቴኑ ነበር፤ በካምፑ ውስጥ አምስት ደቂቃዎች በማይሞላ ቆይታችን ሁሉም ሰው ከካፒቴኑ ጋር ትውውቅ አደረገ ።

በካምፑ ውስጥ የነበረው ውካታና ድንኳናችን ቅርበት ድረስ ሲሰማ የነበረው የአራዊቱ ጩኸት በሚቀጥለው ቀን ለሚከተለው እውነታና ግዳጃችን እንድንነቃ ነው ያደረገን፤ ቀኑም ገፍቶ ነበር። ወዲያውኑ ከሸራው ጣራችን ስር ጥሩ የሆነ የቢጋ አየርና የጋለ አድናቆታችን ወዳተረፈ ዕይታ ወጣን።

የጉና ጉና ካምፕ ያረፈበት ቦታ በጣም የሚወደድና የሚያስደስት ሸለቆ ውስጥ ነበር። በዚህ የተፈጥሮ ውበት የተመሠጠው አንድ የስኮትላንድ ተወላጅ ወጣት፣ ይህ ቦታ የስኮትላንድን የገጠር ቦታ በተክሎቹና በሚገርመው ውበቱ ገልብጦታል አለ።

የሸለቆውን ዙርያ በከበበው ገደል ወደላይ ግማሹ ላይ በአለታማው ደልዳላ ሥፍራ ላይ የሾሆ መንደር ይገኛል፣ የቦታው ስም፣ ጉና ጉና የመጣው ከዚህ መንደር ነው።

ወደላይ እንውጣና ለመጀመሪያ ጊዜ የአቢሲኒያ መንደር ውስጥ እንግባ። ምን አይነት እንግዳ የሆነ ሰፈር ነው? ከሩቅ በጣም የሚያምር የሚመስለው፣ ቀርበው ሲያዩት ግን ደስ የማይል ሰፍራ ነው። ተጠጋግተው የተሠሩ ጠፍጣፋ



ኍና ኍና በማይ ሙና ሸለቆ
(ዋቢ መፅሐፍ ተ.ቁ. 16)

ጣራ ያላቸው የጭቃ ቤቶች እንግዳና ለየት ባሉና ያልተለመደ አለባበስ ባላቸው ሰዎች የተሞላ ነው፡፡ ሰዎች አሉበት በሚባለው ቦታ ሁሉ፣ ጠቆር ያሉ ራሳቸው በቅባት የራሰ ወንዶች፣ ሴቶችና የልጆች ሰብሰብ ነው የሚታየው፡፡ ወጣቶቹ በሙሉ አርቃናቸውን ናቸው፤ በዕድሜ ገፋ ያሉትም ቢሆኑ ለሰሙ ነው ጨርቅ ጣል ያደረጉት፡፡ በመንደራቸው መሀል ሰፍራ በሚገኝ አደባባይ ሰቆም፣ ሁሉም በተቻላቸው መጠን አተኩረው ነበር ያዩኝ፡፡ በዚህ አደባባይ፣ የሰፈሩ ሽማግሌ የተቀመጠበት በማ የሚባል ቦታ አለ፤ ሽማግሌው በሌሎች እለቆች፣ በሽማግሌው ምክትሎች ወይም በዕድሜ ተከታይ በሆኑ ሰዎች ተከቧል፡፡ ደንብ አስከባሪው በሰውየው ቀኝ በኩል ተቀምጧል፤ ንግግር የሚያደርገው ይኸው ሰው ነበር፤ ከሱ አጠገብ ደግሞ ከሳሽ ነው ብዬ የገመትኩት አንድ ወጣት ተቀምጧል፡፡ ፍርድ ቤት ነው ማለት ነው፤ የአቢሲኒያ ሸንጎ፣ እና ችሎት ተይዞ ነበር፡፡ ምንም አንኳን በጣም እንግዳ የሆንኩ ሰው ብሆንም፣ ተሟጋቾቹ፣ ሽማግሌዎቹ እና የችሎቱ ሰዎች በሙሉ በሙግቱ ሰላተኮሩ እኔን ለረዥም ጊዜ እተኩረው አላዩኝም፡፡ ትንንሾቹ ግን ዙሪያዬን ከበው፣ በነዛ ጥቋቁር አይኖቻቸው ያለማቋረጥ አፍጠው ያዩኛል፡፡ ሲጋራዬ የተለየ ትኩረት ነው የሳበው፤ ትንሽ አንኳን አይኔን ባንቀሳቅስ ወይም ጠቀሰ ባደርግ ለነዚህ አቦርጂኒዎች[70] የተለየ ሰሜት ነው የሚፈጥረው፡፡ ሳል ሰሰል፣ ሁሉም በሃሳብና በአትኩሮት ነው የተዋጡት፤ ድምፄ ደግሞ ሌላ የማይነገር ሁኔታ ነው የፈጠረው፡፡ የቆዳዬ ቀለም ደግሞ ምን እንደሆነ ሲፈቱት የሞከሩት ሌላ ነገር ነበር፡፡ የእጆቼ ሁኔታ ደግሞ ከራሳቸው ሰውነት ጋር እያወዳደሩ የተመሰጡበት ነገር ነበር፡፡ እኔ ግን ችሎቱን ረሳሁት፡፡

ተናጋሪው ሰውዬ እጆቹን ዘርግቶ መሬቱን በእግሩ እየተመተመ ወደፊት በመፈናጠር ቃላቶችን ረግጦ እንዲናገር ያደረገው ነገር ምን ይሆን ብዬ ማሰቤ አልቀረም፡፡

የአቢሲኒያኖችን ሸንጎ ዕድሜ ይሰጠው! ከዚያ በኋላ በሠፈሩ ሰው አንዳለ ታጅቢ የጎጆዎችን ውስጥ ሁኔታ በቅርብ ለማየት አመራሁኝ፡፡ ጎጆዎቹ ለየብቻቸው የተሠሩ ሲሆን፣ ግድግዳዎቻቸው ከሰድስት እስከ አሰር ጫማ ከፍታ አላቸው፤ የተሠሩትም በቀይ ጭቃ ነው፡፡ ጣራቸው በቀርከሀ አንጨቶች የሥሩ ሲሆን፣ ላያቸው ላይ ሳር ተደርጎበት ላዩ የግማሽ ጫማ ውፍረት ያለው አፈር ተደምድሞበታል፡፡

---

70 አቦርጂኒዎች በአውስትራሊያ የሚገኙ ጎሳዎች ናቸው፡፡ ፀሐፊው ለምን አቦርጂኒ እንዳላቸው ግልፅ አይደለም፤ ከጥቁረታቸው በስተቀር፡፡ ነገር ግን፣ በፀያፍ አጠቃቀም ጥንታዊ ሰዎች ለማለትም ይሆናል፡፡

በመጠነኛው የጎጆዎች ዙሪያ ባለው ጥላ ስር የሚታዩት በእድሜ የገፉ እያት ሴቶች ሲሆኑ፣ ጥርሳቸው ወልቆ በእድሜ ብዛት ፊታቸው የተጨማደደ ነበሩ፤ እነሱም በእድሜያቸው ከዚህ ቀደም የሚያስታውስቱን ዜማ ሲቆዝሙ ይሰማሉ፤ ዝቅ ባሉት መግቢያ በሮች ደግሞ፣ እድሜያቸው በመቶዎች አመታት የሆኑ ቅድመ አያት ወንዶች ይታያሉ፤ እነሱ ግን በርጋታ ፀጥ ያሉ ናቸው።

ከመንደሩ ሌላው አካባቢ፣ ሰዎች፣ "የምስራች! አሸናፊዎች መጡ" ሲሉ በለማንበት አቅጣጫ ቁጥር ያላቸው ህፃናትና ሴቶች መጡ፤ በአይኔ ዙሪያውን ስመለከት፣ ንቅሳት ያላቸው ጠቆር ያሉ እናቶች በኛ ዙሪያ ተቀምጠዋል። እናቶቻቸውን በማየት የተበረታቱ፣ ወደ ሃምሳ የሚሆን ከብ ዐይን ያላቸው ትንንሽ ልጆች አቧራው ላይ ይቧርቁና ይንከባለሉ ጀመር፤ አቧራውንም ቁልል ፒራሚድ ወይም ቤት የመስለ ቅርፅ ይሰሩበታል፤ ይህም የኛ ልጆች በባህር ዳርቻ ባለ እሸዋ እንደሚጫወቱት አይነት ነበር። ፣ ምንም እንኳን ብዙ ጥቅም ባይኖረውም የሚታየውን ሁሉ ነገር ካየሁ በኃላ፣ የግድ መመለስ ነበረብኛና ጋራውን ወርጄ ስጨርስ፣ ካፒቴኑ እንደገና ለዛሬው መንገድ፣ ለጉዞ ተዘጋጅቶ ሲጠብቅ አገኘሁት።

በችኮላ፣ አስቢው ሠራተኛዬ አሊ ያፈላልኝን ሻይ ጠጥቼ፣ ሲጋራ ለኩሼ ፈረሴ ላይ ወጣሁና ያንን የሚያስደስት እይታ ያለውን ጉና ጉናንና ሸለቆውን ተሰናብቼ ተጓዦችን ተከተልኩ።